# የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር

## (ት.ዴ.ት)

## ፕሮግራም

መጋቢት 1999 (March, 2007) ተሻሽሎ የወጣ

# ትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር
# ፕሮግራም

*መግቢያ*

*ጥንታዊትዋ ኢትዮጵያ የየራሳቸው ሥልጣኔና ሥርዓተ-መንግስት መስርተው ይተዳደሩ ከነበሩት ጥቂት ቀደምት ሃገሮች ኣንድዋ እንደሆነች ሃውልቶችዋ፣ ፊደሎችዋ፣ ልዩ የሆነ የዘመን መቍጠርያዋ፣ በራሷ ፊደልና ቋንቋ በብራና ተዘግበው ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉት አኩሪ የታሪክ መዛግብቶቿ፣ አርኪዮሎጂስቶች በቁፋሮ እያገኙዋቸው ያሉ የጥንት ህንፃዎችና ቁሳቁሶች ህያው ሆነው የሚኖሩና ጥንታዊ ገናናነትዋን የሚመሰክሩ ቀዋሚ መረጃዎች ቢሆኑም ዛሬ እጅግ ወደ ኋላ ከቀሩት የዓለም አገሮች ውስጥ አንዷ አገራችን መሆኑዋ አሌ ሊባል የሚቻል ጉዳይ አይደለም። አገራችን ያላት እምቅ የተፈጥሮ ሃብትና በመሰደድ ላይ የሚገኘው ብቃት ያለው የሰው ኃይል ባገባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል ሥርዓት በማዋቀር ኣጥጋቢ እድገት ማምጣት የሚቻል ሆኖ እያለ፣ የመልካም ኣስተዳደር እጦት ባስከተለው ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ምክንያት ዜጎች በድህነትና በፍትሕ እጦት የሚጐሳቍሉባት፣ ገዢዎች ግን ብዙኃኑን  በመርገጥ ለብቻ የሚያዝናኑባትና የሚፈነጩባት ሀገር ሆናለች።*

*አብዛኞቹ የዓለም አገሮች የኢኮኖሚ እድገት፤ መረጋጋትና ሰላም ባገኙበት ባሁኑ ሰዓት አገራችን በዓለም ላይ በጣም ኋላ ቀር ተብለው ከሚታወቁት አገሮች ተራ ተመድባ ትገኛለች። ከጥንት ጀምሮ ህዝባችንን ሲያሰቃዩ የኖሩ ልዩ ልዩ በሽታዎች፣ ድርቅ፣ ወረርሽኝ፣ ረሀብ፣ መሃይምነት፣ ጦርነት፣ … ወዘተ ዛሬም አሉ። እንዲያውም አንዳንዶቹ ችግሮቻችን ተባብሷል። የአገራችንን ህልውና የሚያናጉ ከባድ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና፣ ፖለቲካዊ ቀውሶች ከተከሰቱ ዓመታት ያስቆጠሩ ቢሆንም፣ በኢትዮጵያ በየተራ እየመጡ ያለፉት መንግሥታት ይህንን አስከፊ ክስተት ለመለወጥ ሙከራ አላደረጉም። የተወሰኑ ሙከራዎች ተደርገውም ከነበረ የህብረተሰቡን ጥያቄ ለመመለስ የማይችሉ ጥገናዊ ከመሆን አልፈው የአገራችንን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ሥር-ነቀል በሆነ መልኩ ሊቀይሩ የሚችሉ አልነበሩም፣ አይደሉምም::*

*ወደ ኋላ መለስ ብለን የአገራችን ያለፉት ሃምሳ ዓመታት ታሪክን ስንገመግም  በየተራ እየመጡ የሄዱት ገዥዎቻችን የየመንግሥታቸውን የሥልጣን ዕድሜ ለማራዘምና መደባዊ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ በሰፊው ህዝብ ላይ ያሳረፉት ፍርደ ገምድልነት አገርና ህዝብን ከመጒዳት አልፎ፣ መጨረሻ ላይ እነሱን ራሳቸውን ከፈጠሩት ሥርዓት ጋር አብረው ተውጠው ምልክት ሳይተዉ ወደማይቀረው መቃብራቸው ሲወርዱ አይተናል። የፈጠሩዋቸው የሰቆቃ ሥርዓቶች አገራችንና በህብረተሰባችን ለእንግልት ዳርጓል። በዚህ ምክንያትም እነዚህ ገዥዎች በራሳቸውና ባገራቸው ላይ አሉታዊ ክስተቶችን ጋብዟል። የሚያስገርም ነገር ቢኖር እስካሁን ድረስ በተከታታይ የምናያቸው አገዛዞች አንዱ ከሌላው ድክመት ለመማር አለመቻሉ ነው። ደርግ የአፄ ኃይለስላሴን ሥርዓት ቢኮንንም ራሱ ከኰነነው ሥርዓት የተሻለ ሆኖ ለመገኘት አልቻለም። አለመሻል ብቻ ሳይሆን አገርንም ትውልድን በመግደል ካወገዘው የአፄ ሥርዓት በእጥፍ ድርብ የባሰ ሆኖ ተገኘ። በዛው ምክንያትም በህዝብ ተተፍቶ፣ ተነጥሎ ሲያዘግም ከቆየ በኋላ የማይቀረውን የፖለቲካ ሞት ተጎንጭቷል። አንዳንድ ናፋቂዎች ቢኖሩትም ላይመለስ ተቀብሯል። ደርግ የአፄ ኃይለስላሴን ሥርዓት ያውግዝ እንጂ በተግባር ሲታይ ከአፄዩ አገዛዝ በባሰ መልኩ የህዝቦችን መብት ረግጧል። ስለተጠላም ሂዷል። የዛሬዎቹ ገዥዎችም ቢሆኑ የደርግን ሥርዓት በማውገዝና በማጥላላት የሀቀኞች መፈክር*

እያሰሙ የህዝብ ወገንተኛ መስለው የህዝባዊ ትግል አጋር ነን በማለት በአስመሳይነት ለ17 ዓመታት በተካሄደው የትጥቅ ትግል ውስጥ የተከፈለው ህዝባዊ መስዋእትነትን ከመጤፍ ባለመቁጠር ይኸው ዛሬ በሥልጣን ኮረቻ ላይ በመውጣት አገርና ህዝብን በማሰቃየት ላይ ናቸው። እነሱ ትላንት ደርግን ያወገዙበትና ከደርግ ጋር በአፈሙዝ የተፋለሙበት አቋም ከደርግ ሞት በኋላ እነሱ ራሳቸው የደርግ ተግባራት ባለቤት ሆነው ለመውጣት በቅቷል።

የኢትዮጵያ ህዝቦች አምባገነን መንግሥታትን በማስወገድ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማስፈን ባካሄዱት ረጅምና መራራ ትግል የከፈሉት መስዋእትነት ከፍተኛ መሆኑ ማንም ሊዘነጋው የሚችል አይደለም። ይህም ሆኖ ግን ዛሬም ለህዝብ ጥያቄይዎች ምላሽ የመስጠት ፍላጎት የሌለውና ካለፉት ዘመናት ጥፋቶች መማር ያልቻለው በኢህአዴግ የሚመራው አገዛዝ የህዝቦችን የዘመናት ትግል በመናቅ አገሪቱን ወደ ባሰ ችግርና ወደ ሌላ የጦርነት አዙሪት መልሶ እየከተታት ይገኛል። ይህ አገዛዝ ለመብትህ መከበር ታገልኩልህ ብሎ ለሚሸነግለው የትግራይ ህዝብም ሆነ የአጠቃላዩ የኢትዮጵያ ህዝቦች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በመርገጥና በማፈን አገራችንና ህዝቦቻችን ህይወት ላይ ዙርያ ምላሽ ችግሮችን አስፍነዋል። ከመቸውም በባሰ በህዝቦች መካከል መቃቃርና ግጭትን አስፋፍቷል። በዚህም ለብዙ ህዝብ ሕይወት መጥፋት ምክንያት ሆኗል።

በህዝቦች መካከል መቃቃርና ግጭት ከተለኮሰ፣ እድገትና በሰላም ኣብሮ መኖር የሚታሰብ ጉዳይ ሊሆን አይችልም። የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር ይህንን አደገኛ ኣዝማምያ ለመቀልበስና በህዝቦች መካከል የነበረው ሰላማዊ ዝምድናና መተሳሰር እንዲቀጥልና፣ በዜጎች መካከል ሰላም እንዲሰፍን በህዝቦቻችን ዘንድ መቀራረብና መተማመንን ማስፈን ይቻል ዘንድ እንደ ድልድይ ሆኖ ለመታገልና ለማታገል፣ በዚህም ፍትሕና ዘላቂ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በኢትዮጵያችን ለመመሥረት በሚደረገው ትግል የበኩሉን ግዳጅ ለመወጣት ዝግጁ መሆኑን ይገልጻል።

ት.ዴ.ት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚቋቋም መንግሥት የኢትዮጵያ ህዝቦች ሙሉ መብታቸውን ያለገደብ ተጠቅመው በዴሞክራሲያዊ መንገድ በሚያፀድቁት ሕገ-ህዝብ (ሕገመንግስት) ስልጣን ተረክቦ የሚመራ ሲያጠፋም የሚወገድ መሆን አለበት ብሎ ያምናል፣ ለተግባራዊነቱንም ይታገላል። የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ቀርበው የህዝብ ድምጽ ለማግኘት በነፃና በእኩልነት የሚወዳደሩበት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር በጽኑ ይታገላል። የብዙኃን ፓርቲ ዴሞክራሲ፣ በህዝብ ምርጫ የብዙኃኑን ድምጽ ያገኘ አንድ ፓርቲ ወይም ጥምር ፓርቲዎች ሥልጣን ተረክበው ሕገ-መንግሥቱ በሚፈቅደው የጊዜ ገደብ ተጠናቅቆ አዲስ ምርጫ እስኪካሄድ ድረስ አገርን ይመራል/ሉ ብሎ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር ያምናል ለተግባራዊነቱም ይታገላል። ሰዎች በፖለቲካዊ አመለካከት በሚለያዩበት ህብረተሰብ ውስጥ የብዙኃን ፓርቲ ዴሞክራሲ መኖር አስፈላጊነት የሚያጠያይቅ አይደለም። ዜጎች ፍላጎታቸውን የሚያሟላላቸው የፖለቲካ ድርጅት መኖሩና ይህ ፓርቲም በሕግ ከለላ ሥር የሚሠራ መሆኑን ከተገነዘቡ፣ ፍላጎታችንን ያሟላል ከሚሉት ወገን ጋር በመሰለፍ በሰላም ታግለው የአገሪቱ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት በሰላማዊ መንገድ የሥልጣን ሽግግር እንዳለ ስለሚያውቁ ወደ ጦርነት የሚያመሩበት ምክንያት አይኖርም። ይህ ሲሆን ህብረተ-ሰቡ በሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱ ላይ እምነት ስለሚኖረው በአገራችን የተለመደው ለሥልጣን የሚደረገው የትጥቅ ትግል ይዘጋል። በመሆኑመ የሚነሱ ቅራኔዎችን በውይይት ለመፍታት የሚያስችል የውይይት በር ይከፈታል።
ሌላው የሚታየው የፖለቲካ ችግር የብሔር/ብሔረሰቦች ጥያቄን የሚመለከት ነው። ያለፉት የኢትዮጵያ መንግሥታት በፈጠሩት የፍትሕ መዛባት ምክንያት እየተካረረ

የመጣው የብሔሮች ቅራኔ አሁንም ዘላቂ መፍትሔ አላገኘም። ቅራኔው ገዢዎች የፈጠሩትና ከፋፍለው ለመግዛት የተገለገሉበትና ዛሬም እየተገለገሉበት የሚገኝ ቢሆንም የተፈጠረው ልዩነት በተለያዩ የአገሪቱ ህዝቦች መካከል ከመጠራጠርና ከጥላቻ እስከ መገዳደል ድረስ የዘለቀ ሁኔታ ተከስቶ መጥፎ ስሜቶችን ፈጥሯል። ዛሬ የነበረው ታሪካዊ ዝምድና እንዳልነበረ፣ ያልነበረው ደግሞ እንደነበረ ተደርጎ የሚቀርብበት ሁኔታ መከሰቱን እየተመለከትን ነው። ሕወሓት/ኢህአዴግም ችግሩን በመረዳት የተፈጠሩትን ልዩነቶች በመፍታት ፈንታ እያባባሳቸው ይገኛል። በተለይ የሚያስገርመው ደግሞ አገዛዙ በህዝቦች መካከል የታዩትን ቅራኔዎች አንዱን በመደገፍና ሌላውን በማጥላላት ችግሩ እንዲባባስ ራሱ የችግሩ አካል ሆኖ መገኘቱ ነው።

ህዝቦች በዚህና በሌሎች መሰል መጥፎ አስተዳደራዊ ችግሮች ተሰቃይተውና ተማረው መፍትሄ ያገኙ እየመሰላቸው መፍትሔ የማይሆነውን የመገንጠልን ጥያቄ ወደ ማቀንቀን እንዳያመሩ የኢትዮጵያ ዴሞክራት ኃይሎች ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። የጭቆና መፍትሄ ታግሎ ጭቆናን ማስወገድ እንጂ መገንጠል ሊሆን ከቶ አይችልም። የኢትዮጵያ ህዝቦች በብሔር ብሔረ-ሰብ ስም ቢገነጣጠሉ ለችግሮቻቸው መፍትሄ ተገኘ ማለት እንዳልሆነ በእውን ሊረዱት ይገባል፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችም ይህንን የማስረዳት ሓላፊነት የነሱ ሸክም መሆኑ ምን ጊዜም ሊዘነጉት አይገባም እንላለን። ሌላው አደጋ የመገንጠል ጥያቄን እናስተናግድ ቢባል የጥያቄው ማቆምያ ድንበር የት እንደሆነ ለይቶ ለማወቅ ፈጽሞ የማይቻል መሆኑ ላይ ነው። ጥያቄው የእኩልነት፣ የመከባበር፣ ባጠቃላይ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መጠበቅ ሆኖ መፍትሄውም ለነዚሁ መብቶች መከበር ታግሎ ፍጻሜ ላይ ማድረስ ነው። እንደነዚህ ጥልቀት ያላቸው የፖለቲካ ችግሮችንም በመገንዘብና በብሔሮች መካከል መሰረታዊ ቅራኔ እንደሌለ በመረዳት የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር (ት.ዴ.ት) በብሔሮች እኩልነትና መከባበር የተመሠረተ የኢትዮጵያ አንድነት መርሆ ላይ የጸና አቋም ይዞ ለእውንነቱ በተግባር ይታገላል።

ኢኮኖሚያዊ ኋላ ቀርነት ከሰው ልጅ የተዛባ አስተዳደር ተዛምዶ የሚፈጠር ክስተት ነው። አልፎ አልፎ የሚከሰት የተፈጥሮ አደጋ አሉታዊ ሚና መጫወቱ የታወቀ ቢሆንም መልካም አስተዳደር እስከተመሠረተ ድረስ ችግሩን በቀላሉ በመወጣት ቀጣይነት ያለው ዕድገት ማስመዝገብ እንደሚቻል የሚያጠራጥር አይደለም። አገሮች በንቅዘትና በወታደራዊ እሽቅድድም ውስጥ ሲዘፈቁ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታየው የኢኮኖሚ ዕድገትና ውድድር ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ተሳታፊ ለመሆን ስለማይችሉ የዓለማችን ኢኮኖሚያዊ ግሥጋሴ ጥሎአቸው ይሄዳል፣ በተለይ ደግሞ ለውጭ ገበያ ሊውል የነበረው የአላቂና ጥሬ እቃዎች ምርት መቀነስ ከገበያው ያስወጣቸውና ጭራሹን መሻገት ይጀምራሉ። በተወሰኑ አገሮች ላይ የተከሰተው የኢኮኖሚያዊ አውታሮችን መፈራረስ፣ የአስተዳደር መዛባትና አገባብ የሌለው የሀብት አጠቃቀም ያስከተለው ቀውስን ስናጤን፣ ዛሬም የአገራችን ኢኮኖሚ እያሽቆለቆለ፣ ሥራ-አጥነትና በሽታ ተዛምቶ፣ ግጭቶች በየቦታው ተለኩሰው ስናይ አገራችን የደረሰችበትን አደገኛ ሁኔታ በእውን ያሳስበናል።

በርግጥ ለዘመናት በሽታና ረሀብ የአብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ የዕለት ኑሮ ሆኖ ቆይተዋል። በአሁኑ ወቅት ደግሞ ሥራ አጥነቱም ይሁን በሽታው በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ መጥቷል። የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ከነዚህና ተያይዘው ከተከሰቱት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ለመላቀቅ አጣዳፊ መፍትሔ መሻት ያስፈልገዋል። መፍትሔዎቹም በህዝብ ልበ-ሙሉ ተሳትፎና የህዝቡ አለኝታ ያገኘ ቆርጠ የተነሳ መንግሥት ይሆናሉ። በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የአገሪቱ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ላይ መሠረታዊ ለውጥ ማምጣቱ ወይም መቅረፉ ቀርቶ እያባባሰው ለመሆኑ ተጨባጭ ሃቁ ያረጋግጣል። ይህ መንግሥት ሌላው

ይቅርና ሥራ አጥነትን በመቀነስ ፈንታ በ"ብቃት ማነስ" በማሳበብ የሥራ ልምድ ያላቸውን ሠራተኞች ያለምንም ካሣ ወይም ተተኪ የሥራ መደብ ከሥራ ገበታቸው እያባረረ ህብረተሰቡን እያቆሰለ ይገኛል። የሥራ አጡ ቁጥርም በየቀኑ በእጥፍ እየጨመረ በመሄድ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል እየነካ ነው። የስራ አጡ ቁጥር መበራከት ራሱ አደገኛ ብጥብጥ ሊቀሰቅስ እንደሚችል ኣጠያያቂ አይደለም።በሌላ በኩል ደግሞ ምሁሩና ባለሙያው መጥፎ አስተዳደር በፈጠረበት ጫና ተማሮ የሚወዳት አገሩን ጥሎ በመኮብለል የባዕድ አገሮች ልማትና ብልፅግና ላይ ገንቢ አስተዋፅኦ ስያበረክት ይታያል።

ያለንበትን ሁኔታ ለማየት ኣንዳንድ ኣኃዞችን ብንጠቅስ ተገቢ ይመስለናል። ኢትዮጵያ የመጨረሽ ድሃ ከሚባሉት ኣገሮች ኣንዷ ነች። የሰው ዕድገት መመዘኛ (The Human Development Index) በሚባለው ኢትዮጵያ ከ177 ኣገሮች ውስጥ በ170ኛ ደረጃ ያስቀምጣታል። ከኢትዮጵያ በታች ያሉት 7 ዝቅተኛ ኣገሮችም በጦርነት ውስጥ የቆዩ ወይም ያሉ እንደ ቻድና ሴራሊዮን የመሳሰሉት ናቸው። ኢትዮጵያ 81% ህዝቧ በዝቅተኛ የድህነት ደረጃ ማለትም በቀን ከ 2 የኣሜርካ ዶላር በታች የሚኖር ነው። 70% የሚሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ንጹህ ወሃ የማያገኝ ነው።

ይህ ለዘመናት የሻገተና መሻሻልን ያላሳየ ኢኮኖሚ ላይ ፈጣን ለውጥ ለማምጣትና ተያይዘው ያንሰራሩት ኣያሌ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ለመፍታት ትክክለኛውን አቅጣጫ ማወቅና መያዝ እራሱ በህብረት ካልሆነ በስተቀር በተናጠል የማይቻል እጅግ ከባድና ውስብስብ ሥራ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ከጅምሩ ትክክለኛ አቅጣጫ ካልተያዘ መድረሻው አይታወቅም። ሥር የሰደዱትን ዘርፈብዙ የሃገራችን ችግሮች ለመቅረፍ በቅድሚያ የመፍትሄው አጠቃላይ ኣቅጣጫ በህብረት መንደፍና መዋቅሩን በጋራ መዘርጋት ይኖርብናል። ይህን አገር አድን መፍትሄ መሰረት ለማስያዝና የሰው ልጆችን ችግር ለማቃለል የሚረዱትን ፖሊሲዎች ያለምንም ቀኖናዊነት በተግባር ለመተርጎም ት.ዴ.ት. ቆርጦ ተነስተዋል። የኣፈጻጸሙ መመርያም ቀጥሎ በሚቀርበው ዝርዝር የፕሮግራም ይዘት ተገልጸዋል።

# ክፍል I

## የፖለቲካ ፕሮግራም

1. ዓላማው የኢትዮጵያ ህዝብ የስልጣን ምንጭና ባለቤት መሆኑ የሚረጋገጥበት፣ የሕግ የበላይነት የነገሰበት፣ የዜጎች ግላዊም ይሁን ስብስባዊ መብቶች የሚከበርበት ዘለቄታነት ያለው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መመስረት ነው።

2. በሁሉም ፖለቲካ ሃይሎች፣ ሙያና ሲቪክ ማህበራት እንደዚሁም ሕገ-መንግስታዊ ጠበብት ተረቆ በሞላው ህዝብ ተሳትፎ የጸደቀ ሕገ-መንግስት (ሕገ-ህዝብ) የሃገሪቱ የበላይ መመርያ ይሆናል።

3. ሶስቱ መሰረታዊ መንግስታዊ ኣካላት፣ ሕግ አውጪ፣ ተርጓሚና፣ ኣስፈጻሚ፣ ሕገ-ህዝቡ ለያይቶ በሚሰጣቸው የስራ ድርሻ ተገድበው ይሰራሉ። ሕግ ተርጓሚው የፍርድ አካል ከማንኛውም ኣካል ተጽእኖ ፍጹም ነፃ ሆኖ ፍትህ እንዲነግስ ያደርጋል።

4. የብዙኃን ፓርቲ ፓርላሜንታዊ ሥርዓት ሆኖ፣ ሁለት ዘርፍ ያለው ምክር ቤት (ፓርላማ) ይቋቋማል። አንዱ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የህዝብ ብዛትን መሠረት ያደረገ ውክልና ይኖረዋል። ሁለተኛው የፌደራል ምክርቤት ከየራስ ገዝ ክልሎች በእኩልነት የሚወክል ይሆናል። እነዚህንም ወኪሎቹን ህዝብ ነፃና ፍትሐዊ የሆነ ምርጫን በመጠቀም በቀጥታ ይመርጣቸዋል። የሁለቱም ዘርፎች ስልጣንና መብት እንዲሁም ያላቸው ግንኙነት በህግ ይወሰናል።

5. መሠረታዊ የሆኑ ዴሞክራሲያዊ መርሆዎችን ማለትም የመናገር፣ የመሰብሰብ፣ ሀሳብን በጽሑፍ የመግለጽ ነጻነቶችን፣ ገለልተኛና ሁሉን ያለ አድልዎ ሊያሳትፍ የሚችል የመገናኛ ብዙኃን መኖር፣ ሰላማዊ ሰልፍና የሥራ ማቆም አድማ የማድረግና በነጻ የመደራጀት መብቶች በተግባር ላይ ይውላሉ።

6. ሰዎች በሙያም ሆነ በሲቪክ ማህበራት ከፓርቲና ከመንግሥት ቁጥጥር ነፃ ሆነው የመደራጀት መብቶቻቸው ይከበራል።

7. የብሔሮችና ብሔረሰቦች የራሰን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ያከበራል።

8. የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ከሚለያዩዋቸው ይልቅ የሚያስተሳስርዋቸው የጋራ ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ማህበረ-ኢኮኖምያዊ ሃረጎች ስለሚያይሉና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ህዝቦች ተለያይተው ሳይሆን በአንድነታቸው የሚያገኙት ጥቅም ስለሚበልጥ፣ በመፈቃቀድ ላይ ለተመሠረተ አንድነት ይታገላል።

9. በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙትን የማነኛውም ብሔር ብሔረሰብ ባህልና ታሪክ ማስፋፋትና ማቀብ በሕግ ይደገፋል ያከበራል።

10. ት.ዴ.ት የራስገዝ ክልሎች የብሔር ክልል ሳይሆን፣ የክልሎችን ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና የህዝቦችን አንድነት በሚያጠናክር መንገድ በቂ ጥናት ተደርጎ እንዲቀናጅ ይደግፋል።

11. ሃይማኖትና መንግሥት የተለያዩ ሆነው ኣንዱ በሌላው ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ መግባት በሕግ የተከለከለ ይሆናል። የእምነት ነፃነት ያከበራል።

## ክፍል II

## የኢኮኖሚ ፕሮግራም

1. እንደ ኢትዮጵያ ባሉት ህዋላ ቀር አገሮች ውስጥ መንግሥት ከማንም ግለሰብ የበለጠ በብሔራዊ ሃብት ላይ የማዘዝ ችሎታና የማስተባበር ኣቅም ስላለው ሃገሪቷ ውስጥ ሊኖር ለሚገባው ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከፍተኛ ሚና መጫወት ይጠበቅበታል። ስለዚህ የመንግሥትና የግል ካፒታል በብቃት ተዋህዶ በጥቅም ላይ በመዋል የአገሪቱን ኢኮኖሚ እንዲገነባ ይደረጋል።

2. የግል ኢንቨስተሮች በንብረታቸው ላይ ለሚኖራቸው መብት ዋስትና ይሰጣቸዋል። ሆኖም ንብረቱ ለብሔራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት በሚኖረው አስተዋፅኦ ወደ መንግሥት ንብረትነት ቢዛወር ለባለንብረቱ ሙሉ ካሣ ይከፈላል ።

3. የኢትዮጵያ መልክኣ ምድርና የህዝቡ ኑሮ ሲታይ በሁሉም ቦታ ኣንድ ወጥ የሆነ የመሬት ይዞታ ፖሊሲ ለመቅረጽ ኣያስችልም። በመሆኑም ት.ዴ.ት የግል፣ የጋሪዮሽ እንዲሁም የመንግሥት የመሬት ይዞታ ፖሊሲ ሊኖር ይችላል ብሎ ያምናል። ፖሊሲው ተጠቃሚው ህዝብ ባለሙያና መንግሥት በተሳተፈበት የሚቀረፅ ሲሆን፣ ፖሊሲው የኢትዮጵያ ነባራዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በተያያዘ ለአገሪቱ ጥቅምና ለምርት ዕድገት የሚመች እንዲሆን ያስፈልጋል።

4. የኢንዳስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲያድግ መንግስት በቅድሚያ ከሃገር ውስጥ ቀጥሎም ከውጭ ሃገር ባለ ሃብቶች ጋር በመዋዋል ወይም ዋስትና ያለው ፈቃድ በመስጠት የኣጭርና የረጅም ጊዜ እቅዶቹን ተግባር ላይ እንዲውሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

5. አብዛኛው የህዝባችን ክፍል አርሶ አደር እንደመሆኑ ለእርሻ ክፍለ ኢኮኖሚው ዕድገት አስፈላጊ ትኩረት ይሰጣል። በምግብ ራስን የመቻል ፖሊሲ ቅድሚያነት ያገኛል።

6. ኣርብቶ ኣደሩ ህዝብ የከብት እርባታውን ስራ የተሻለ እድገት እንዲያሳይ መንግስት ከህዝቡ ጋር በመመካከር ሰፋፊ እቅዶች ነድፎ ተግባር ላይ ያውላል።

7. የህዝብ ብዛትና የመሬት ጥበት በሚታይበት ኣካባቢ ልዩ የስራ መስኮች በመክፈት ወይም በጥናት የተደገፈና በህዝቡ የታመነበት ሰፈራ በማዘጋጀት ችግሩ እንዲቃለል ያደረጋል።

8. የሓይል ምንጮች፣ ደኖች፣ የማእድንና የውሃ ሃብት የመሳሰሉ የተፈጥሮ ሃብቶች መንግስት እየተቆጣጠረ ላገሪቱ ኣጠቃላይ እድገት ያውላል።

9. መብራት ሓይል፣ ፖስታ፣ ቴሌፎን፣ አውራ ጎዳና የመሳሰሉ አበይት ግልጋሎት ሰጪ ተቅዋማት ለሃገሪቱ ዘላቂ እድገት በሚያመች መንገድ የግል ባለሀብቶችንም ጭምር በሚያሳተፍ መልኩ የሚመራ ይሆናል።

10. በእርሻም ሆነ በእንዱስትሪ እንዲሁም በህዝባዊ ግልጋሎት የግል ኢንቨስትሮች ሃብታቸውን አሰማርተው የሚያድጉበት አስተማማኝ በሕግ የተደገፈ ደንብ ስራ ላይ ይውላል።

11. በሃገር ውስጥና ከውጭ ሃገሮች ጋር የሚደረገው የንግድ እንቅስቃሴ የአገራችንን እድገት በሚያጎለብት መልኩ ነጻ ሆኖ እንዲስፋፋ መንግስት ያበረታታል።

12. በመላው የሃገሪቱ ክፍል የተመጣጠነ እድገት እንዲኖር በልማት ወደኋላ የቀሩትን አከባቢዎች አስፈላጊ ድጋፍ በመስጠት እድገታቸው እንዲፋጠን ያደርጋል። በድህና ሀብታም መካከል ያለውን ልዩነት ለማጥበብ የሚያስችል ፖሊሲ ይነደፋል።

## <u>ክፍል III</u>

## <u>የአከባቢ ሀብት ጥበቃ ፕሮግራም</u>

1. ኢትዮጵያ በዓመት ወደ 1.5 ቢሊዮን ቶን አፈር በውኃ እየታጠበ የሚባክንባት አገር ሆናለች። ይህም የሆነው በህዝብ መጨመር ምክንያት የነበረው ደን በየጊዜው እየተመነጠረ በመጥፋቱ ነው። ስለሆነም አለአገባብ የሚደረገው የደን ምንጠራን ለመቆጣጠር የሚያስችልና የጠፋውንም በዕፀዋት ተከላ ለመተካት የሚያስችል ሀገራዊ ፖሊሲ ይነድፋል።

2. በደን መጥፋት የሚጠፉ የዱር አራዊቶቻችንን ከመጥፋት ለማዳን የሚያስችል የትምህርት ፕሮግራም በማዘጋጀት በመደበኛ ትምህርትም ሆነ በመገናኛ ብዙኃን ትምህርቱ ለህዝብ እንዲደርስ ያደረጋል።

3. በአገራችን ውስጥ የብዝሀ-ሕይወት (biodiversity) ጥበቃን ለማጠናከር የሚያስችል በጥናት ላይ የተደገፈ ፖሊሲ ይነደፋል።

4. አገራችን የምትከተለው የኢኮኖሚ ፖሊሲ እርሻን ብቻ ያተኮረ ሆኖ መቀጠል አይችልም። ከእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ጋር አብሮ ጎን ለጎን የሚያድግ እንዱስትሪ ያብባል። ይህ በራሱ የአከባቢ አየር ብክለት ያስከትላል። በመሆኑም የሚገነቡ እንዱስትሪዎች የአከባቢ አየር ብክለትን ለመቆጣጠር በሚያስችል መንገድ ከተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ጋር ተቀናጅቶ እንዲስፋፋ ይደረጋል።

## ክፍል IV

## ማህበራዊ ጉዳይ ፕሮግራም

1. የኢትዮጵያ ህዝብ በታሪክ ሂደቱ ያዳበራቸው ገንቢና አኩሪ ልምዶች፣ ቅርሶችና የስነ-ጥበብ ውጤቶች ተጠብቀው እንዲኖሩና እንዲዳብሩም አስፈላጊ እንክብካቤ ያደረጋል።

2. በፆታ፣ በሃይማኖት፣ በዘርና በብሔር . . ወዘተ ላይ የተመሠረተ ማንኛውም ዓይነት ልዩነትን በማስወገድ ለእኩል አገልግሎት እኩል ክፍያ ዋስትና ይሰጣል።

3. የሃገሪቱ አጠቃላይ እድገትን የሚያቀላጥፍ፤ በጎ ባህልን የሚያዳብር፤ የህዝቡ መሰረታዊ ፍላጎትን ያካተተ ሥርዓተ ትምህርት ተቀርጾ ተግባር ላይ ይውላል።

4. ሁለተኛ ደረጃ ድረስ ለመማር የሚያስችል ነፃ የትምህርት ዕድል ለማቅረብ አስፈላጊ ጥረት ያደረጋል ። የህዝቡ ኢኮኖምያዊ ደረጃ እስኪሻሻል ድረስ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርትም በነጻ የሚሰጥበት ሁኔታ ይመቻቻል።

5. ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዳብሮ ህዝቡን የእድገት ተጠቃሚ የሚያደርግ የጥናትና ምርምር ማእከላት እንዲስፋፉ ያደረጋል።

6. ህክምናና ከበሽታ መከላከልን የሚያጠቃልል ብቃት ያለው የጤና አገልግሎትና ትምህርት እንዲሰጥ ያደርጋል። የጤና ጥበቃ አገልግሎት በሃገሪቱ ገጠሮችና ከተሞች እንዲስፋፉ የሚስችል አስፈላጊ እርምጃዎች ሁሉ ይወሰዳል።

7. ባህላዊ መድሃኒትና የህክምና ጥበባት ከዘመናዊ ህክምና ተቀናጅቶ አገልግሎት ላይ የሚውልበት ዘዴ ተጠንቶ ተግባር ላይ ይውላል።

8. ሁሉም አከባቢዎች ባህላቸውን ለማዳበርና ለማስተዋወቅ ይበረታታሉ። የመንግሥት ድጋፍ ያለምንም አድልዎ ለማግኘት ሁሉም መብት ይኖራቸዋል ።

## ክፍል V

## የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ

1. የኢትዮጵያ ሉኣላዊነትን፣ የህዝብዋ አንድነትንና መሰረታዊ መብቶቿን በማስከበር ላይ የተመሰረተ የውጭ ጉዳይ መርህ ይከተላል።

2. በሌላ ሃገር ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ ያለመግባት ፖሊሲ ይኖራል ።

3. የተባበሩት መንግሥታትና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አባልነትን በመቀጠል ዓለም አቀፍ ሕጎችን በቅንነት ያከብራል ።

4. ከልዩ ልዩ አገሮች ጋር በእኩልነትና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ይደረጋል ።

5. ከማንኛውም አገሮች ጋር የተፈረሙ የአገራችንን ጥቅም አሳልፎ የሚሰጡ ውሎች ሁሉ ተሠርዘው የአገራችንን ዘላቂ ጥቅም በሚያስከብሩ ወሎች እንዲተኩ ያደረጋል።

## ክፍል VI

## ስለ ሃገራዊ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባር

በኢትዮጵያ ለሰላምና እድገት ቅድመ ሁኔታ የሆነው ዘላቂ ዴሞክራስሲያዊ ሥርዓትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሰፊ መሰረት ያለው የዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ትብብር አስፈላጊ ነው ። በአሁኑ ወቅት በአገራችን የግንባር አስፈላጊነት ከምን ጊዜም በላይ ወሳኝ እየሆነ በመምጣቱ የተለያዩ ኢትዮጵያዊያን ኃይሎች በመለስተኛ ዴሞክራሲያዊ ፕሮግራም ሥር እንዲተባበሩና የሃገር ግንባታው በጋራ እንዲጀምሩት ት.ዴ.ት ጥሪ ኣቅርበዋል ። በግንባር ምስረታ ብቻ ሳይወሰንም፤ የድርጅቶች ጋጋታ ተቀንሶ ኢትዮጵያ የሚያስፈልጉዋትን የተወሰኑ( 3 ወይም 4 የሚሆኑ) በሃገራዊ መርሆች ላይ የተወሃሄዱ ሃገር ኣቀፍ ፓርቲዎች እንዲፈጠሩ ጥሪ ኣቅርቦ ለተግባራዊነቱ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። ለህብረቱም ይሁን ለውህደቱ መነሻ ነጥብ ይሆን ዘንድ ከዚህ በላይ የተገለጸው የፖለቲካ ፕሮግራምም ቀርቧል ። ት.ዴ.ት ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች ጋር ሁሉ ውይይትንና መቀራረብን ብቻ ሳይሆን ውህደትንም ይሻል ።

መጋቢት 1999 ዓ.ም. (March 2007)